የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር 7 አይሳኢታ 09ፎ	በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት	2nd Year No. 7 AYSAITA,2001

ማውጫ

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ _____ ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር ፯/፻፱፻፺ፎ ዓ.ም

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር የክልሉን ኢኮኖሚ በሚገባ ለማምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ በግንት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን፣

በልዩ ልዩ የልማትና አስተዳደር መስኮች የተሰማሩ የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ድርጅቶችና ማህበራት የገንዘብ አስተዳደር ተገቢውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት የተከተለ የገቢ አሰባሰባቸው የወጪ አፈቃቀዳቸውና የንብረት አስተዳደራቸው የመንግስትን ህግና መመሪያ ተከትሎ የተፈፀመ መሆኑን እቅድና ኘሮግራማቸውንም በቅልጥፍና እና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ በማከናወን የሚጠበቅባቸውን ግብ ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በክልሉ መንግስት አወቃቀር በየደረጃው ክልላዊ መንግስት መስሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች ሊኖር የሚገባውን ተጠያቂነት በማረጋገጥ የዲሞክራሲን ሥርዓት ለማስፈን ኦዲት ዓይነተኛ መሳሪያ በመሆኑ፣

የሀገሪቱን መንግስት አዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲን በሚገባ ተግባራዊ ማድረግ ይቻል ዘንድ በክልላዊ መንግስት ይዞታ ሥር የሚኙ የአስተዳደር የልማትና የአገልግሎት ተቋማትን ብቃት ለመቆጣጠር በተጠናከረና ዘመናዊ በሆነ የኦዲት ተግባር መታገዝ ያለበት በመሆኑ፣

ለዚህ ተግባራዊነት የክልሉን ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ማቋቋም በማስፈለጉ፣ በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 3 ተራ ቁጥር 3-6 መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲/ 09□□ዩ ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1. «የመንግስት መስሪያ ቤት» ማለት በክልሉ መንግስት የተቋቋመ ቢሮ፣ ኮሚሽን፣ ባለስልጣን፣ ጽ/ቤት፣ ተቋም፣ ኤጀንሲ ወይም ማናቸውም ሌላ የክልሉ መንግስት መ/ቤት ነው።
2. «ድርጅት» ማለት በክልሉ መነግስት የተቋቋመና በሙሉ ወይም በከፊል የክልሉ መንግስት የሆነ የማምረቻ የማከፋፈያ አገልግሎት ሰጭ ወይም ሌላ የንግድ ድርጅት ነው።
3. «ማህበር» ማለት በክልሉ መንግስት የተቋቋመ ማህበር የገበሬ ማህበር፣ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር እና ሌሎች ሕዝባዊ ድርጅቶች ናቸው።

3. መቋቋም፣

1. በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ሕገ መነግስት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 3 ተራ ቁጥር 3-6 መሠረት ከዚህ በኋላ «የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት» እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ሠመራ ሆኖ ለስራው አስፈላጊ በሆነ ቦታ ሁሉ ቅርንጫፍ ቤቶች ይኖሩታል።

4. የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ድርጅታዊ መዋቅር፣

የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት አንድ ዋና ኦዲተር፣ መምሪያ ኃላፊዎች፣ ኦዲተሮችና ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል።

5. የመስሪያ ቤቱ ዓላማ፣

1. የክልሉን መንግስት እቅድ በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
2. የክልሉን መንግስት ገንዘብና ንብረት በፌዴራል መንግስትና በክልሉ ምክር ቤት በወጡት ህጐችና ደንቦች መሠረት መሰብሰቡን መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥና የደረሰበትን ውጤት ለክልሉ ምክር ቤት ሪፖርት ማቅረብ፣
3. በክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የፋይናንስና የክዋኔ ኦዲት ማካሄድ፣
4. አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
5. በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩት ለክልሉ መንግስት ሠራተኞች ድርጅቶች ሙያዊ እገዛና ምክር መስጠት፣
6. የክልሉ መንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ የሚመረመርበትን የኦዲት ደረጃ (እስታንዳርድ) ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

7. በክልሉ ሐብትና ንብረት ላይ የእምነት ማጉደል ወንጀሎች ተፈጽመው ሲገኙ ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው አስተያየት መስጠትና የመሥሪያ ቤቱን የሂሳብ አያያዝ የገንዘብ የንብረት አስተዳደር የሚጠናከርበትን ተገቢ አስተያየትና ምክር መስጠት፣

6. <u>ስለ ዋና ኦዲተር አሿሿምና ተጠሪነት፣</u>

1. ዋና ኦዲተር በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማል።
2. ዋና ኦዲተር ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ይሆናል። የክልሉ ምክር ቤት በማይሰበሰብበት ጊዜ ተጠሪነቱ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል።

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የክልሉ የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ስልጣንና ተግባር</u>

7. <u>የክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ስልጣንና ተግባር፣</u>

የክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በሕግ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን የሚያስፈልገው ስልጣን ሁሉ ይኖረዋል። በዚህ አጠቃላይ አነጋገር ሳይወሰን የክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት፣

1. የክልሉ ምክር ቤት ጽ/ቤትን ጨዋሮ የክልሉን መንግስት መስሪያ ቤቶች ድርጅቶችና ማህበራት ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል።
2. የክልሉ መንግስት ከብር 2 ሺህ /ከሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ/ በላይየሚጠይቅ ሥራ ለግል ተቋራጮች ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል።
3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀው ሆኖ ወንጀል ለመፈፀሙ በቂ ፈንጭ ያገኘ እንደሆነ ሥራው የሚጠይቀው ገንዘብ ከብር 2 ሺህ /ከሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ/ በታች ቢሆንም የመንግስት ሥራ ነክ የሆነውን የተቋራጮችን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል።
4. በዚህ አንቀጽ (1)(2) እና (3) በተመለከተው መሠረት ያከናወነው የምርመራ ውጤት እንደነገሩ ሁኔታ ለክልሉ መንግስት ምክር ቤት፣ መስሪያ ቤት፣ ለድርጅቱ እና ለማህበራቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል። የክልሉ ዋና ኦዲተር የምርመራው ውጤት ወንጀል መፈፀሙን የሚያረጋግጥ ከሆነ ወዲያውኑ ለክልሉ ምክር ቤት ሪፖርት ያደርጋል።
5. ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሳብና የንብረት ምርመራ ሥርዓትና ደረጃን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ያወጣል።
6. ማናቸውም የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤት እና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊው የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ምስክርነት ይሰጣል።

7. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የማናቸውም የክልሉ መስሪያ ቤት የውስጥ ኦዲተሮች የመስሪያ ቤታቸውን ሂሳብና ንብረት በመመርመር ውጤቱን እንዲገለጹለት ሊያደርግ ይችላል።

8. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እንደአስፈላጊነቱ ለውስጥ ኦዲተሮች ስልጠና ይሰጣል።

9. አንድ ሂሳብ ወንጀል ባለበት ሁኔታና ታማኝነት በጎደለው አኳኋን መያዙን ለማመን ምክንያት ያለው እንደሆነ ይህንን ሂሳብ በሚመለከቱ ካዝናዎች፣ መጽሐፎች፣ መዘክሮች፣ መዝገቦች፣ ሰነዶችና በሌሎች መረጃዎች እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መዛግብቱ የሚገኝበትን ክፍል የንብረት ክፍሉንና ቤቱን ያሸጋል።

10. የፋይናንስ ቢሮ ስለ ገንዘብና የሂሳብ አጠባበቅ በሚያዘጋጀው ደንብ ላይ አስፈላጊውን ምክር ይሰጣል።

11. ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልሉና የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ጋር በተመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል። የክልሉ መንግስት የኦዲትና የሂሳብ ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል።

12. ከፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት እና ከሌሎች ክልል ኦዲት መስሪያ ቤቶች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል።

13. በክልሉ ዉስጥ በግል የሚሠሩ ኦዲተሮችና የሂሳብ አዋቂዎች በሥራው መስክ ለመሰማራት መቻላቸውን የሚያረጋግጥ የምክክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣ ስለምስክር ወረቀት አሰጣጥ እድሳትና ስለ አገልግሎት ዋጋ ክፍያ ዝርዝሩ የክልሉ የሥራ አስፈፃሚ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>የዋና ኦዲተር ስልጣንና ተግባር፣</u>

8. <u>የዋና ኦዲተር ስለጣንና ተግባር፣</u>

ዋናው ኦዲተር የዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በመሆኑ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 7 ለዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት የተሰጠውን ስልበጣንና ተግባር ይኖረዋል።

1. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (1) (2) እና (3) መሠረት ስለሚከናወነው ምርመራና አጠቃላይ ዓመታዊ ሪፖርቱን ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል።

2. የፋይናንስ ቢሮ የክልሉ መንግስት ያለፈውን በጀት ዓመት ገቢና ወጭ ሀብትና እዳ እንዲሁም የመንግስት ገንዘብ ነክ የሆኑ መረጃዎችን ሂሳብ የበጀት ዓመቱ እንደተጠናቀቀ በተቻለ ፍጥነት ዘግቶ ለምርመራ ለክልሉ ዋና ኦዲተር ይላካል፣ የክለሉ ዋና ኦዲተርም የሂሳብ ዘገባው እንደደረሰው በአራት ወር ጊዜ ውስጥ መርምሮ አጥንቶ ሪፖርቱን ከእነ አስተያየቱ ለቢሮው ይልካለ። ለክልሉ ምክር ቤት በሚያቀርበው ዓመታዊ ዘገባ ውስጥ ሪፖርቱን እንዲካተት ያደርጋል።

3. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ውጤቱን እንዲያውቁ የተደረጉት አካላት የሰጡት አስተያየትና ያቀረቡት ተቃውሞ አጥጋቢ ያለመሆኑን የገመተ እንደሆነ ይህን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው ዘገባ ውስጥ ያስገባል።

4. ተግባሩን በሚገባ ለማከናወን መስሪያ ቤቱን ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል።

5. በክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የመስሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል። ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

6. በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ሕግና ደንብ ውስጥ የተመለከቱትን መሠረታዊ ዓላማዎችን ጠብቆ የክልሉ ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ለመስሪያ ቤቱ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ይቀጥራል ያስተዳድራል።

7. ለሥራ አስፈላጊሆኖ ሲገኝ በቂ መመሪያ በመስጠት የኦዲት ምርመራ እንደአግባቡ በግል ኦዲተሮች ወይም በሌሎች ባለሙያዎች እንዲከናወን ይወክላል። ሥራቸውንም ይከታተላል።

8. በክልሉ ሀብትና ንብረት ላይ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን በማናቸውም ጊዜ ኦዲት ያደርጋል። በቂ ምክንያት ሲኖረው የተጀመረውን ምርመራ ለማቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ ለማድረግ ይችላል።

<u>ክፍል አራት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

9. <u>በጀትና ሂሳብ ምርመራ</u>

1. ለዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ከተፈቀደው በጀት ውስጥ የ 3 /ሶስት/ ወር ድርሻ የሆነውን የሥራ ማስኬጃ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ስም በተከፈተው ሂሳብ ውስጥ በአንድ ጊዜ በቅድሚያ እንዲቀመጥ ያደርጋል።
2. የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ሂሳብ በክልሉ ምክር ቤት፣ ምክር ቤቱ በማይሰበሰብበት ጊዜ በክልሉ ምክር ቤት ርዕሰ መስተዳድር በሚሰየም አካል ይመረመራል።

10. <u>ስለ ኦዲት ስርዓት የጊዜ ገደብ</u>

1. የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት አንድ ሂሳብ ኦዲት ሲያደርግ ለጉዳዩ አስፈላጊ እንደመሰለው አንድ በአንድ በዝርዝር ወይም በአልፎ አልፎ የኦዲት ዘዴ ሊመረምር ይችላል። ቢሆንም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ሂሳቤችን መርምሮ በሚያቀርበው ዘገባ ውስጥ ለእያንዳንዱ ሂሳብ ያመራመሩን ጥልቀት መግለጽ አለበት።
2. የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በሚያከናውናቸው ምርመራዎች ሁሉ ከሚመረመረው የበጀት ዓመት ወደ ኋላ ከሁለት የበጀት ዓመታት ማለፍ የለበትም። ነገር ግን በእርሱ ግምት ወንጀል መፈፀሙን ያመነ እንደሆነ ከተባሉት ሁለት የበጀት ዓመታት ወደ ኋላ አልፎ ሊመረመር ይችላል።

11. <u>የተመርማሪዎች ግዴታ፡-</u>

1. የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ኦዲተሮች ወይም የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ወኪሎች ለምርመራ ጠቃሚና አስፈላጊ የሚመስሏቸውን መጽሐፍት፣ መዘክሮች፣ መዝገቦች፣ ሰነዶችና ሌሎች የጽሁፍና የቃል መረጃዎች ሁሉ ሲጠይቁ የተጠየቀውን ግለሰብ፣ ሠራተኛ ወይም ባለስልጣን በትክክልና በተሟላ አኳኋን ወዲያውኑ የማቅረብ ግዴታ አለበት።
2. የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት እንዲቆጣጠራቸው በዚህ አዋጅ ስልጣን የተሰጠው አካላትን ገንዘብ ወይም ንብረት የተረከበ ወጪ ያደረገ የከፈለ ወይም የሂሳብ ኃላፊ የሆነ ማንኛውም ሰው ሲጠየቅ ሂሳቡን ኦዲት የማስደረግ ግዴታ አለበት።
3. ተመርማሪው መስሪያ ቤቶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፀ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቤችና አስተያየት መሠረት ከ (ሰላሳ) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ

የመውሰድ ግዴታ አለባቸው። እርምጃ ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው።

4. የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ለክልሉ ምክር ቤት በሚያቀርበው ሪፖርት ውስጥ ድክመት የታየባቸው መስሪያ ቤቶች ኃላፊዎች በታዩት ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ወስደው ይህንኑ ለምክር ቤቱና ለዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው።

5. ተመርማሪው መስሪያ ቤት ለኦዲተሮች ሥራ የሚሆን ቢሮ የመስጠት ግዴታ አለበት።

12. <u>የማሳወቅ ግዴታ፣</u>

የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ኦዲት ሲያከናውን በጉዳዩ ላይ ወንጀል መሠራቱን ያመነ እንደሆነ ይህንኑ ለፍትህ ቢሮ እና ለሚመለከተው ኦዲት ተደራጊ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት የበላይ ኃላፊ ማስታወቅ አለበት፣

13. <u>ተጠያቂ፣</u>

ያለበቂ ምክንያት በክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በቀረቡ ኦዲት ሪፖርቶች በተሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶችና ሃሳቦች ላይ በወቅቱ እርምጃ ያልወሰደ ወይም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት መፈፀም ሲኖርበት ለመፈፀም ፈቃደኛ ሆኖ ያልተገኘ ማንኛውም ሰው በዲሲፕሊን ወይም እንደ አስፈላጊነቱ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል።

14. <u>ቅጣት፣</u>

ማንኛውም ሰው፣

1. የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በቀጥታ ወይም በኦዲተሮች ወይም በወኪሎቹ አማካይነት ለምርመራ እንዲቀርብለት የሚጠይቀውን መጽሐፍት መዘክሮች መዛግብት ሰነዶችና ሌሎች የጽሁፍ ወይም የቃል መረጃዎች ያላቀረበ ወይም

2. ለዋና ኦዲተር ወይም ለወኪሎች ሀሰተኛ መረጃ የሰጠ ወይም እውነተኛ መሆኑን ለማመን ምክንያት ሳይኖረው ማናቸውም መረጃ የሰጠ ወይም፣

3. የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ስራ በሚገባ እንዳይከናወን ያሰናከለ፣ እንደሆነ እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ እስራት ወይም ሁለት ሽህ ብር /2ሺህ/ የገንዘብ መቀጫ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

15. ቀደም ሲል የክልሉን ሴክተር መ/ቤቶች ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 6/09□□1 አንቀጽ 0 የክልሉን ዋና ኦዲተር መ/ቤት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ በዚህ አዋጅ ተተክቷል።

16. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ፣</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ _____ ቀን 09ኛ_____

እስማኤል አሊ ሴሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር